# ይፍጠኑ! ነፃ የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠና ዕድል ይህ ውለዎ!

## የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠና በነፃ ስለማግኘት መብት

በኖርዌይ የመኖሪያ ፈቃድዎ በጠቅላላ ለ 300ሰዓትታት ያህል ማለትም፥
♦የኖርዌጅኛ ቋንቋን 250 ሰዓታት እና
♦የህብረተሰብ ትምህርትን 50 ሰዓታት ለመከታተል መብት ይሰጠዎታል።

ስልጠናው በነፃ በሶስት ዓመታት ውስጥ የሚሰጥ ሆኖ ተግባራዊ የሚሆነው፥
♦የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙበት ቀን ጀምሮ ወይም
♦ወደኖርዌይ ህጋዊ ፈቃድ ይዘው ከገቡበት ቀን ኣንስቶ ሊሆን ይችላል።

ማስገንዘቢያ፥ እላይ በተጠቀሱት ሶስት ዓመታት ስልጠናውን ካልጀመሩ ወይም ካላጠናቀቁ ስልጠናውን ከፍለው እንዲማሩ ይደረጋል።

## የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስለመከታተል ግዴታ

የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስልጠናውን በ 300 ሰዓታት የማጠናቀቅ ግዴታ የሚያስፈልገው፥
♦ቀዋሚ የነዋሪነት ፈቃድ እና/ወይም
♦የዜግነት መብት ለማገግኘት ማመልከቻ ለማቅረብ ይሆናል ።

ይህን ግዴታ በስልጠና ምዝገባ ወቅት ዕድሜዎ 55 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ ግን ተፈፃሚነት ኣይኖረውም።

ከስልጠናው ግዴታ ነፃ ለመሆን ማመልከት የሚችሉት ፥
♦የኖርዌጅኛ ወይም የሳሚኛ ቋዋንቋዋ በቂ ችሎታ ያለዎት መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ፥
♦በተለይ የጤና እክል ወይም ሌላ ኣሳማኝ ምክንያት ካለዎት ይሆናል።

## ተጨባጭ መረጃ

ስልጠናውን ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ መረጃ ከፈለጉ ከተመዘገቡበት የህዝብም ዝገባ ፅህፈት ቤት ኣቅራቢያ በሚገኘው የማዘጋጃ ቤቱ የመሰልጠኛ ማእከል በኣካል ቀርበው ማመልከት ይችላሉ። የምዝገባ ቀን ማጠናቀቂያ ወይም መብትዎን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት እና መረጃ ከፈለጉ ከማሰልጠኛ ማእከሉ ጋር መገናኘት ይችላሉ ። ተጨማሪ መረጃ ከ www.imdi.no እና www.udi.no ማግኘት ይችላሉ።